# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
## ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail:-[illegible]@ethionet.et


ቁጥር: Ref. No መአ/3/40/2003
ቀን Date 15/02/2003

## <u>ጋዜጣዊ መግለጫ</u>

## <u>ከ</u>

## <u>የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/</u>

## <u>ረሐብን ማጥፋት የተሳነው ኢህአዴግ</u>

## <u>መድብለ ፓርቲን ለማጥፋት ተያይዟል!</u>

የአንድ መንግሥት ኃላፊነት ሀገርና ሕዝብን ማስተዳደር ሲሆን የዜጐችን መሰረታዊ ፍላጐት ማለትም መጠለያ፣ ምግብና ልብስ ማሟላት የመጀመሪያ ግዴታው ነው፡፡ ዛሬ በዓለም ላይ የሚገኙ መንግሥታት ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን ሲያስተዳድሩ በቅድሚያ ለዜጐቻቸው መሰረታዊ ፍላጐት አሟልተው ለሌሎች ሀገሮችም ሲተርፉ ይታያሉ፡፡ ከሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶቹ ደግሞ ምግብ ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ አይደለም፡፡ መንግሥትም ለዚህ ቅዱስ ዓላማ ከፖሊሲና ስትራቴጂ መንደፍ ጀምሮ ለተግባራዊነቱ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አጀንዳ ነበር፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የእርሻ ድርጅት /FOA/ም ይህንኑ አንገብጋቢ አጀንዳ የተቋቋመበትን ወቅት ለማስታወስ ሁልጊዜ በየዓመቱ ኦክቶበር 16 ቀን ያከብረዋል፡፡ መንግሥታትም ይህን ቀን አብረው ሲያከብሩና ሲያስቡ ቢታዩም ቀኑን ማክበሩ ብቻ በቂ አይደለም፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጐች በምግብ እጥረት እየተሰቃዩ እያለ የዓለምን የምግብ ቀን አክብሮ መዋሉ ለተራ የፖለቲካ ፍጆታና ለዲፕሎማሲያዊ ትርፍ ካልሆነ በስተቀር ፋይዳ የለውም፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብታም ብትሆንም በየዘመኑ ሥልጣን ላይ በሚመጡ ገዢዎችዋ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲና የመልካም አስተዳደር ችግሮች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጐች በረሐብ እየተሰቃዩ ለምግብ ርዳታ ተዳርገው መታየት በዓለም አቀፍ ደረጃ መገለጫችን ሆኖ መቀየቱ በእጅጉ ያሳዝነናል፡፡

ኢህአዴግ ገና ወደ ሥልጣን ሲመጣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በቀን ሶስት ጊዜ እንዲመገብ አደርገዋለሁ ቢልም ሶስት ጊዜ ለመመገብ ያሚያስችሉ የኤኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ነድፎ ከመንቀሳቀስ ይልቅ የራሱን የሥልጣን ጊዜ ለማራዘም በሚያደርገው ጥረት በአፄ ኃይለሥላሴ እና በደርግ ዘመናት ከታየው የርሃብተኛ ቁጥር በላይ በኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመን መመዝገቡን በርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ይፋ አድርገውታል፡፡ ይባስ ብሎ ገዢው ፓርቲ ሀገራችን ባለ ሁለት ዲጂት የኤኮኖሚ እድገት አስመዝግባለች በማለት ለምግብ ዕጥረት የተጋለጡትን የዜጐቻችንን ቁጥር ለመደበቅ ሲውተረተር ማየት አሰልቺ ድራማ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ሰሞኑን የወጣው የሂዩማን-ራይትስ-ዎች መግለጫ እንደሚያስረዳው እና እኛም ከየክልሉ በደረሰን መረጃ መሠረት እንደምናውቀው ገዢው ፓርቲ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከለጋሽ ሀገሮች የመጣውን የልማትና ሰብአዊ ርዳታ ሌሎችን በማግለል ለራሱ አባላቶችና ደጋፊዎች ብቻ በማከፋፈል ለፖለቲካ ሥልጣን ማራዘሚያ ማዋሉ ከአንድ መንግሥት የማይጠበቅ በእጅጉ አሳፋሪ ተግባር መፈፀሙ ግልጽ ነው፡፡

ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ በሀገራችን ያለውን የእርሻ መሬትም ለሀገራችን ገበሬዎችና ኢንቨስተሮች በመስጠት በምግብ ራሳችንን እንድንችል ከማድረግ ይልቅ ለውጭ ባለሀብቶች የአበባ አምራችነት መሰጠቱ ቅድሚያ ሊሰጥ የሚገባውን የዜጐቻችን የምግብ ዕጥረት ማቃለል ወደጐን መተው የመንግሥታችን ኃላፊነትን መዘንጋት መስሎ ይታየናል፡፡

በደርግ ጊዜ ከተከሰተው የምግብ እጥረት በላይ የምግብ ፈላጊዎች /የዕርዳታ ፈላጊዎች/ በአሁኑ ሰዓት መታየቱ የመንግሥታችንን ኃላፊነት አለመወጣት ብቻ ሳይሆን ለዜጐች ያለውን ተቆርቋሪነት ዝቅተኛ መሆን ያሳየናል፡፡

በየአመቱ ኦክቶበር 16 የምግብ ቀን ብሎ ማክበሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚዘይደው ፋይዳ ባለመኖሩ መንግሥት ተቃዋሚዎችን ለማዳከም ሌት ተቀን ከሚሰራ ይልቅ ዜጐቻችንን ከረሐብ ለመታደግ ያላሰለሰ ጥረት ሊያደርግ እንደሚገባ ፓርቲያችን ያሳስባል፡፡

የምግብ እጥረት ለማስወገድ መንግሥት የተሳሳተ የኤኮኖሚ ፖሊሲውን መቀየር እንዳለበት አበክረን እያሳሰብን ይህ ሊሆን የሚችለው ኢህአዴግ ኃላፊነት ተሰምቶት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጡትን አስተያየት መቀበል አስፈላጊ መሆኑን እየገለጽን፣ እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን በማለት አንድ አቅጣጫ መከተል ሕዝባችንን ለባሰ ርሐብ ሊያጋልጠው እንደሚችል ለማስረገጥ እንወዳለን፡፡

መንግሥት የአንድን ፓርቲ የበላይነት ዘለዓለማዊ ለማድረግ ሲባል፣ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴውን ለዚህ ዓላማ ማዋሉ፣ ከለጋሽ መንግሥታት እና አባሎች የሚገኘውን የእርዳታ ስርጭት አድሎአዊ ባልሆነ ለሁሉም ተረጂ ዜጐቻችን በእኩልነት እንዲከፋፈል ከኢህአዴግ መንግሥት የሚጠበቅ ሲሆን ይሄም ሳይደረግ ቀርቶ ሌሎች ተቃውሞአቸውን ባቀረቡ ቁጥር አግባብ ያልሆነ የመከላከያ መልስ ማቅረቡ ለዜጐቻችን ማሕበራዊና ኤኮኖሚያዊ ችግሮች መፍትሄ ባለመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወዲሁ ሊታገለው የሚገባ አካሄድ መሆኑን እየጠቆምን የምግብ ቀንን ማክበር ብቻ ሳይሆን የተራቡ ወገኖቻችንን አስተውለን ከችግሩ የምንላቀቅበትን አሰራር በአስቸኳይ መቀየስ ያስፈልጋል ሲል የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ያሳስባል፡፡

ጥቅምት 10 ቀን 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ